# በሲያትል የኢትዮጵያውያን ማሕበር (ኢሲኤስ)

የኢትዮጵያውያን ማሕበር

(ኢሲኤስ)

መተዳደሪያ ደንብ

አድራሻ

**8323 Rainier Ave S.**

**Seattle WA 98118**

ECS Bylaw Draft

## የኢትዮጵያውያን ማሕበር በሲያትል የመተዳደሪያ ደንብ

እኛ በሲያትልና አካባቢው የምንኖር የኢትዮጵያ ተወላጆች የብቻችን የኛ የሆነ ብርቅዬ ታሪካችንና ባህላችንን በመረዳት፤ በሲያትል በርካታ ልዩ ልዩ ቋንቋና ባለብዙ ባህል ህዝብ መኖሩን ስላስተዋልንና፣ የራሳችንን ባሕልና ቋንቋ ባለቤትም ስለሆንን ራሳችንን የሚወክል ማሕበር ማስፈለጉን በመገንዘብ፣ይህን ማሕበር መሥርተን በሚከተሉት ደንብና ሥርዓት መልክ እንዲተዳደር አድርገናል። ማሕበሩ ሊያከናውናቸው የታቀዱትን አላማዎች በቀለጠፈ ሁኔታ ከግቡ እንዲያደርስ ያመች ዘንድ የቀድሞውን መተዳደሪያ ደንብ እንደሚከተለው አሻሽለነዋል።

### አንቀጽ 1

የማሕበሩ ስም

የኢትዮጵያውያን ማሕበር (ኢሲኤስ) በሲያትል ይሆናል።ከዚህ በኋላ “ማሕበሩ” ወይም (ኢሲኤስ) እየተባለ ሲጠቀስ፤ይህንኑ ማሕበራችንን መሆኑ ይታወቃል።

አድራሻው 8323 Rainier Ave S
Seattle, WA 98118

### አንቀጽ 2

የማሕበሩ መርሕና ዓላማ

2.1 የ(ሲአኤስ) ማሕበሩ ተቀዳሚ ተግባር የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ያለ ችግር በቀላሉ ወደ አሜሪካ የአኑዋንዋር ዘይቤ እንዲሸጋገሩ የሚያስችለውን ዘዴ ለማመቻቸት ነው።

ከዚህም በላይ ማሕበራችን (ኢሲአኤስ) በፒውጂት ሳውንድ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን-አሜሪካውያን፤አኩሪ የትውልድ ታሪካቸውን፣ባሕላቸውን እንዲያወቁና ለተተኪው ለ ትዉልድ እና ሌላውም ሁሉ እነዲያሳውቁ ይረዳል፤ ያበረታታል።

የማሕበሩ ራዕይ

2.2 ኢሲኤስ በሲያትልና አካባቢው፣ ኢትዮጵያዊነትና ጨዋነት ተጣምሮ የምንኮራበት ባሕላችን ተጠብቆ፣ የማሕበሩ አባላት እርስ-በርስ ተከባብረው፣በጋርዮሽ የሚሳተፉበት፣ ማሕበር በወግ በመጠበቅ፤

ሀ) በሲያትልና አካባቢው የሚኖሩ የማሕበሩ አባላት ሁሉ፣ በተቻለ አቅም የተከበረ እና፣ የጨዋነት ሕይወት እንዲኖሩ ማረጋገጥ፤

ለ) ተከታዩን ተተኪ ትውልድ በመምከር፣ በቀና አቀጣጫ በመምራት፤ ምሁር፣ ሕግ-አክባሪና ጨዋ የሕብረተ-ሰብ አባል እንዲሆን በትጋት ማነፅ፤

ሐ) ከትምህርት ቤቶች፤ ከመንግሥት አካል ድርጅቶችና፤ ከህክምና ሰጭ-ኣጋር ድርጅቶች፤ ከሥራ አስቀጣሪ- ወኪሎች ሁሉ ዘላቂ-ወዳጅነት በመፍጠር፤ ለአባላቱ አሰፈላጊ የሆኑት፤ ትምህርት፣ሙያ-ሥልጠና፣የጤና አገልግሎቶች ያለችግር እንዲገኙ መሟገትና መርዳት፤ዋና ዎቹ ናቸዉ::

ECS Bylaw First Draft

## 2.3 የምንመራባቸው መሠረታዊ -ሃሳቦች

ማሕበራችንን፣ግልፅ በሆነ መልክ፣ ለሃላፊነት ተጠያቂነት ባለው ሥርዕት ማስተዳደር ይሆናል። በጾታ፤ በእድሜ፤ በብሔር፤ (በሓይማኖት)በእምነት፤ በፖለቲካ አቋም በአባላት መሃከል ያሉትን ልዩነቶች አክብረንና ተቻችለን በህብረት እንራመዳለን

# አንቀጽ 3

## የአስተዳደር መዋቅር

## የማሕበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

በማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት፣ ለኮሚቴ አባላት ወይም ለአባላት ከተሰጠው ሞብት በስተቀር የሥራ አፈጻጸምና የአስተዳደር ሃላፊነቱ የይድሬክተሮች ቦርድ አባላቱ ከዚህ በኃላ “ቦርዱ” እየተባለ በሚጠራው የቦርዱ ይሆናል። የቦርዱም የሥራ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይከናወናል።

3.1 ቁጥራቸው 15 (አሥራ አምስት) የሚሆኑ፣ ብቁ የሆኑ የቦርድ አባላት በዓመታዊ ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ጊዜ ለማሕበሩ በቦርድ አባልነት ለተመደበው ጊዜ እንዲያገለግሉ ይመረጣሉ። ለማሕበሩ ቦርድ ለመመረጥ ብቃት የሚያሟሉ ሁኔታዎች ቦርዱ ለሥራ ቅልጥፍና እንደሚያመቸው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይሆናል፤

3.2 ቦርዱ ማሕበሩ የሚሰጠውን አገልግሎቶች አዘውትሮ ይመረምራል፣ የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞችን አስተውሎ ያጸድቃል።

3.3 የማሕበሩን የዓመት ሥራ ማስፈጸሚያ ባጀቱን ከታቀዱት የአገልግሎት ፕሮግራሞች ክንውን ጋር እያስተያየ፣የሥራውን በደንብ መካሄድ መርምሮ ያጸድቃል።

3.4 በየሦስት ወራት፣ ሊሰሩ የታቀዱትን የማሕበሩን ፕሮግራሞችና የሚሰጡትን አገልግሎቶች በተመደበው በጀት መሠረት በትክክል መፈጸሙን በማነፃጸር ይመረምራል።

3.5 ከባለአደራ ቦርድ ጋር በመመካከር፣ ስለ ሲያትል ከተማ በ **8323** ደቡብ ሬኒየር አቬኑ ላይ ስለሚገኘው (የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማአከል) (የኢሲኤስ) የማሕበሩ ንብረት አስመልክቶ፣ ያሉትን ሕጋዊ ውሎች፣እዳዎች፣ ብድርና የስምምነት ውሎች በሙሉ ይመረምራል።

3.6 የማሕበሩ (የኢሲኤስ)ሥራ አፈፃጸም እንደሚያስፈልገው መጠን፣ የቦርዱ አባላት ስብሰባ በዋና ፀሓፊው ጠሪነት ቢያንስ በወር አንድ (1) ጊዜ ይሆናል። ከቦርድ አባላቱም መሐከል 51% (51-ከመቶ) በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።

ECS Bylaw First Draft

3.7 ከቦርድ አባልነት ለመልቀቅ የምትሻ/የሚሻ አባል፣ የስንብት ደብዳቤዋን/ውን ለፕሬዚዳንቱ በማሳወቅ፣ እራሱ/ሷ ፕሬዚዳንቱም ከሆነ፣ ለዋና ፀሃፊው በማሳወቅ፣ ቦርዱ በቀጣዩ ስብሰባ እንዲያየው ይደረጋል።

3.8 የቦርድ አባላትን ልዩ ስብሰባ ለመጥራት፣ የሚሹ ሥስት (3) ወይም ኪዚያም የሚበልጡ አባላት ቢኖሩ፣ ይህንኑ ጥያቄ በጽሁፍ እስከአቀረቡና ቦርዱ ሊወያይበት የሚገባውን ጉዳይ በትክክል እስካስታወቁ ድረስ፣ አሥር (10) ቀናት አስቀድመው ከታወጀ፣ የቦርድ አባላት ልዩ ስብሰባ መጠራት ይቻላል።

3.9 በማንኛውም ምክንያት በግል ፍቃዳቸውም ሆነ በሌላ ሰበብ አምስት (5) የሚሆኑ የቦርዱ አባላት ከቦርዱ ቢሰናበቱ፣ እስከሚቀጥለው ጠቅላላ የአባላት ጉባዔ ድረስ ጊዜያዊ ተተኪ ቦርድ አባላት በጎደለበት መተካት ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ አምስት (5) በላይ ቦርድ አባላት በድንገት ከለቀቁ ግን፣ ቦርዱ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ አስቸኳይ ጠቅላላ ስብሰባ መጥራት ይኖርበታል።

3.10 ቦርዱ የማሕበሩ እቅዶችና ዓላማዎች እንዲሳኩ ለማድረግ፣ የማሕበሩን ንዋይ፣ ገንዘብ ሃብትና ንብረት እንደአስፈላጊነቱ ሁሉ ያዝበታል። ቦርዱ ከባንክም ሆነ ከሌላ አበዳሪ አካል ለማሕበሩ ሥራ መበደር ወይም እዳ መክፈል ውል መፈረም ሥልጣን ይኖረዋል፤ ስለሚከናወነው የሥራ አፈፃጸም ሁሉ ለጠቅላላው ጉባዔ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

3.11 ቦርዱ ለማሕበሩና ለቅርንጫፍ አካሎች ሁሉ ሠራተኞች ይቀጥራል፣ያሰናብታል፣መተዳደሪያ ደመወዛቸውንም ይወስናል።የማሕበሩ ሠራተኞች አስተዳደር ደንብና መመሪያ ሁሉ በሚገባ ተግባራዊ መሆኑንም በወግ እየመረመረ፣ የማሕበሩ ተቀጣሪ የሆኑት በሙሉ በሥርዓት መቀጠራችውንና በአግባብ መሰናበታቸውን ያረጋግጣል።

3.12 ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እያቋቋመ የሚጠበቅባቸዉን ተግባርና ለሥራቸዉ ሚያስፈልጋቸውን ሥልጣን በመዘርዘር፣ ከጊዜ ወደጊዜም አንደአስፈላጊነቱ እያያሻሻለ ይመስርታል። የማሕበሩ ልዩ ኮሚቴዎች በሙሉ በቀጥታ ለኢሲኤስ (ለኤክዜኩቲቭ ኮሚቴ) ሥራ-መሪ ኮሚቴ ተጠያቂ ይሆናሉ።

3.13 ቦርዱ የማሕበሩን ጉዳዮች እንዳሉ በሙሉ ማስፈፀምና ማስተዳደር ሃላፊነቱ ነው።ለሥራውም አፈፃጸም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ የማሕበሩን የዉስጥ ደንቦች ማሻሻልና መለወጥ፣ መሰረዝና ሀላፊዎችንም የመቀየርና የመተካት ሥልጣን አለው።

3.14 ማንኛውም የቦርድ አባል፣ ሦስት ተከታታይ የቦርድ ስብሰባዎች ላይ ሳይገኝ ከቀረ፣ ወይንም ከዓመቱ የቦርድ ስብሰባዎች ገሚሱን ካልተሳተፈ፣ ለመቅረቱም/ለመቅረትዋም አጥጋቢ ምክንያት ከሌለው/ላት እንደማይኖር ተቆጥሮ፣ በምትኩ ሌላ አባል ይተካበታል።

ECS Bylaw First Draft

3.15 ማንኛውም የቦርድ አባል በበቂ ምክንያት፣ሥራ በመበደልም ቢሆን በንዝህላልነት እንደሚገባው ድርሻውን ሥራ ሳይሠራ ውዝፍ ቢያበዛ፣ ወይም የማሕበሩን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ከሆነ፣ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከተገኙት ዓባላት በሦስት-አራተኛው (3/4) በተደገፈ ድምፅ ከቦርድ አባልነት እንዲታገድ ሊወስንበት ይችላል። በቦርድ እባላቱም የተወሰደው የማስወገድ ውሳኔ ለተጠያቂው አባል በተመዘገበ ፖስታ ፣ በአድራሻው ስብሰባው ከመደረጉ አምስት (5) ቀናት አስቀድሞ በጽሁፍ ሊላክለት ያስፈልጋል።

## አንቀጽ 4

### ሹማምንት

4.1 የማሕበሩ አስተዳደርና ሥራ አመራር ሹማምንት፣ ማለትም፣ ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንት፣ ዋና ጸሃፊ፣ ገንዘብ-ያዥ (ዓቃቤ-ንዋይ) የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ፣ ሲሆኑ፤ ሌሎችም ቦርዱ የሚሾማቸው ሀላፊዎችም ይሆናሉ። ቦርዱ እነዚህን የሥራ መሪዎች ሹማምንት ከአባላቱ መሃከል መርጦ መሾም ይችላል።ይህም ቦርዱ ያደረገው ሹመት፣ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ለጠቅላላው የማሕበሩ አባላት በይፋ በደብዳቤ መታወቅ ይኖርበታል።

4.2 ፕሬዚዳንት

(ሀ) ፕሬዚዳንቱ የማሕበሩ ዋና ሥራ-መሪና አስተዳዳሪ ባለሥልጣን በመሆን፣ በሚገኝበት/በምትገኝበት ጠቅላላም ሆነ የቦርድ ብቻ ስብሰባ ሁሉ፣ በሊቀ-መንበርነት ይመራል/ትመራለች። ፊርማ የሚያስፈልጋቸውን ሰነዶችም ሆኑ፣የብድርም ውሎች፣ የከፍያ መፈቀጂያ ቼክ እና ደረሰኞችን ሁሉ መፈረም አለበት/ባት። ከዚህም ሌላ፣ በየጊዜው ቦርዱ የሚመድበውን ተጨማሪ ተግባራት ሁሉ በሃላፊነት ይፈፅማል/ትፈጽማለች።

(ለ) ፕሬዚዳንቱ/ትዋ ለልዩ ኮሚቴዎች ሊቀ-መንበር መሾምም ሆነ ማስመረጥ ይችላል/ትችላለች። ይህንንም ለማከናወን በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ እስካልተጠቀሰ በስተቀር፣ ድምፅ የሌለው የኮሚቴ አባል ብቻ ይሆናል/ትሆናለች። ፕሬዚዳንቱ/ትዋ ስለልዩ ኮሚቴ መመሥረት ለቦርዱ በማስታወቅ፣ ለየኮሚቴው በሊቀ-መንበርነት የታጩትን በማቅረብ ቦርዱ ተመራጮችን እንዲያጸድቅ ይጠይቃል/ትጠይቃለች።

(ሐ) በቦርዱ በግልጽ ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ ፕሬዚዳንቱ/ትዋ በማንኛውም የማሕበሩ ጠቀሜታ ድርሻ ወይም ማሕበሩ (ኢሲኤስ) በሚሳተፍበት የአክሲዮን ድርጅቶች ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ፤ አለያም በመልክት ደምጽ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል/ይኖራታል።

(መ) ፕሬዚዳንቱ/ትዋ አዲስ የፕሮግራም ሃሳብ አቅራቢ (አፍላቂ) የሆኑ ግለ-ሰብ አባላትን፣ ልዩ-ተግባር ቡድን ወይም ኮሚቴ ውስጥ ገብተው እንዲሠሩ ለመሾም ይችላል/ትችላለች።

ECS Bylaw First Draft

(ሰ) ፕሬዚዳንቱ/ትዋ ሥራ-አመራር (ኤክዜኩውቲቭ) ኮሚቴውን ስብሰባ ይጠራል/ትጠራለች። ይህንኑ የሥራ-አመራር ኮሚቴም በሊቀ-መንበርነት ይመራል/ትመራለች።

## 4.3 ምክትል ፕሬዚዳንት

ምክትል ፕሬዚዳንት ለፕሬዚዳንቱ/ትዋ የተሰጡትን ሥልጣንንና ሃላፊነቶች ሁሉ ይዞ፣ ፕሬዚዳንቱ/ትዋ በሌለበት/በሌለችበት ጊዜ በፕሬዚዳንቱ/ትዋ የተጠየቁትን ተግባራቱን በሙሉ ሃላፊ የሥራ መሪ በመሆን ያከናውናል/ታከናውናለች።

## **4.4** ዋና ጸሐፊ

(ሀ) በማሕበሩ ቦርድ ስብሰባዎችና፣ በጠቅላላው የአባላት ስብሰባ እየተገኘ ቃለ-ጉባዔዎችን አጥርቶ በወግ ይመዘግባል/ትመዘግባለች።

(ለ) ለጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ጥሪም ሆነ ለማሕበሩ ሥራ አፈፃጸም ሁሉ፣ ያሚላከውን ጥሪም ሆነ መልክት የሚልከው ይይዛል/ይጠዋና ፀሐፊው ይሆናል። የማሕበሩን የስብሰባ መዛግብትና፣ ማህተም በሚገባ ጥንቃቄና ከበሬታ በመያዝ ይጠብቃል። በተጨማሪም ሌላ ቦርዱ የሚሰጠውን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

(ሐ) ጸሐፊው የቋሚ ኮሚቴዎችን ቃለ-ጉባዔ እየሰበሰበ በሥርዓት መዝግቦ ይይዛል።

(መ) የሥራ ዘመኑን የፈጸመ ጸሓፊ፣ አዲስ ተመርጦ ለሚረከበው ቦርድ የመጀመሪያውን ስብሰባ በሁለት ሣምንታት ውስጥ ጠርቶ፤ ስብሰባውን በሥርዓት አካሂዶ ማሰረከብ ሃላፊነት አለበት።

## **4.5** ገንዘብ-ያዥ **(**ዓቃቤ-ንዋይ**)**

(ሀ) ገንዘብ-ያዡ፣ የማሕበሩን ገንዘብና ጠቃሚ ንዋይ ሁሉ እየተቀበለ በጥንቃቄ ይይዛል። በደንብ የገንዘብ ማስገቢያ ሰነዶችን በሥርዓቱ መሠረት፣ ቦርዱ በመረጠው ባንክ ገንዘቡን ያስቀምጣል።

(ለ) ለገንዘብ ከፍያ መጠየቂያ የቀረቡትን ሰነዶች በሥርዓቱ እያመሳከረ፣ የተከናወኑት ሥራዎች ሁሉ ቦርዱ ወይም የቦርዱ ወኪል ሹማምንት ፈቅደው ያጸደቋቸው መሆናችውን ያረጋግጣል ። የሥራውን በደንብ መፈጸምና የግዢዎችን እርገጠኛነት ተከፋዩን ሂሳብ ካረጋገጠ በኋላ፤ ገንዘብ -ያዡ/ዥዋ ተገቢውን ከፍያ በጊዜው መከፈል አለበት/ባት።

(ሐ) ገንዘብ-ያዡ/ዥዋ የማሕበሩን ገንዘብና ንዋይ ሁሉ በሥርዓት በመቆጣጠር፤ የሂሳቡን መዛግብት በሙሉ እያስተካከለ/ለች በሚገባ ጥንቃቄ ይጠብቃል/ትጠብቃለች። በየሶስት ወር ገንዘብ-ያዡ/ዥዋ የማሕበሩን ገቢና ወጪ በወግ በማወራረድ፤ ጠቅላላው የአባላት ስብሰባ በመረጠው (በሂሳብ መርማሪ) የተጣራ ሂሳብ ዘገባ ያቀርባል/ታቀርባለች።

ECS Bylaw First Draft

(መ)  ገንዘብ-ያዥ የበጀትና የሂሳብ ኮሚቴዎችን በሊቀ-መንበርነት ይመራል/ትመራለች።

## 4.6 የሕዝብ-ግንኙነት ሹም

የሕዝብ-ግንኙነት ሹም የሚከተሉት ተግባራትን ማስፈጸም ሃላፊነት ይኖርበታል

ሀ)  የ(ኢሲኤስን)ማሕበሩን ዓላማዎች፣ እርምጃዎች፣ እቅድ ሥራዎችና የወደፊት ፕሮገራሞችን ለሌሎች በማሳወቅ፡ ማሕበሩ የሚያድገበትን መንገድ በመሻት፣ አዳዲስ አባላት እንዲመጡና ማሕበሩ እንዲያድግ ይጥራል።

ለ)  በቦርዱና በፕሬዚዴንቱ/ትዋ የጸደቁትን ጋባዥ ጽሑፎችና፣ የሚበተኑ ሀትመቶችን እያዘጋጀ ለኣባላትም ሆነ፣ ለሕዝብ እንዲዳረሱ ያሰራጫል።

ሐ)  የማሕበሩን ዋነኛ ዓላማዎችን፣ በውጥን ያሉ እቅዶችን ለሕዝብ በይፋ ያሳውቃል።በዚህም መልክ ለማሕበሩ የወደፊት እባላት እንዲሆኑ በመጋበዝ፣ በሚቻለው መጣር ይኖርበታል።

መ)  ባሕላዊና ሕዝብ የሚያሰባስብ ዝግጅቶችን በማቀናበር፣የማሕበሩ እባላትም ሆኑ ሌሎችም ሰለማሕበሩ ያላቸው ግንዛቤ መለካም እንዲሆንና ማሕበሩ እንዲጠነክር በማሰተማር ይደግፋል።

## 4.7 የቦርድ ዳይሬክተሮች ምርጫ

ሀ)  የቦርዱ ዳሬክተሮች ቁጥራቸው አስራ አምስት (15) የሆነ አባላት ይኖሩታል። የአገልግሎት ዘመናቸውም ለአራት (4) ዓመታት ብቻ ይሆናል። ለማስባጠር ያመች ዘንድ፤ ሰባቱ አባላት ለመጀመሪያው ሁለት ዓመታት ሲያገለግሉ፤ ከዚያ በኋላ ግን ጠቀላላው ጉባኤ ሰባት ወይም ስምንት ተጨማሪ አባላትን በየሁለት ዓመታት እየመረጠ ይተካል።

ለ)  ቢያንስ ሁለት ዓመታት ቋሚ አባል ሁነው የቆዩ አባላት፣ ለቦርድ አባልነት እጩ ሆነው ለመታጨት ብቃት ይኖራቸዋል። በጠቀላላው የአባላት ስብሰባ ላይ፣ እያንዳንዱ አባል ለየአንዳንዱ ምርጫ፣ አንድ ድምጽ ብቻ የመስጠት መብት ይኖረዋል።

ሐ)  ተተኪነታቸውን የሚቀጥለው ጠቅላላ ስብሰባ እስከሚያጸድቀው ድረስ፤ በአንቀጽ 3.9 በተጠቀሰው መሠረት፤ ማንኛም ተተኪ አባል ፣ የተካውን/ችውን አባል የሥራ ዘመን መፈጸም አለበት/ባት።

# አንቀጽ 5

ባለ-አደራ ቦርድ

ECS Bylaw First Draft

## አመሠራረት (አወቃቀር)

**5.1** ዘጠኝ (9) አባላት ያሉበት ባለ-አደራ ቦርድ በሚከተለው መልክ ይመሠረታል።

ሀ) በመሠረቱ የ(ኢሲኤስ) ዳይሬክተሮች ቦርድ ሁለቱ እባላት ማለትም፡ ፕሬዚዳንትና፣ ም/ፕሬዚዳንት ሥራውን ስለሚመሩ፣ በቀጥታ የባለ-አደራ ቦርድ አባላት ይሆናሉ። ኢመማ እባላት ከአባላቱ መሃከል፣ አምስት አባላት ለባለ-አደራ ቦርድ ይመርጣሉ። የዲሬክተሮች ቦርድ ደግሞ ሁለት (2) ኢትዮጵያዊነት የሌላቸውን፣ ለማሕበሩ (ኢሲኤስ) ይበጃሉ የሚላቸውን አሜሪካውያን ባለ-አደራ ቦርድ አባል እንዲሆኑ ሰማቸውን ያቀርባል።

ለ) የባለ-አደራ ቦርድ በቀጥታ ተጠያቂነቱ ለኢሲኤስ ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል። የባለ-አደራ ቦርድ ከዲሬክተሮች ቦርድ ጋርና፣ ከሌላው የማሕበሩ አካል-ክፍሎች ጋር በመመካከር በ **8323** ደቡብ ሬንየር አቬኑ፤ ሲያትል ዋሽንግተን **98118** አድራሻ ሰለሚገኘው ንብረት ጥበቃና ደህንነት እና እንክብካቤ ተባብሮ ይሠራል። ንብረቱንም በሚገባ አስከብሮ፣በወግ ያስጠብቃል።

**5.2** የባለ-አደራ ቦርድ ምርጫና የሥራ ዘመን፤

ሀ) አምስት (5) እጩዎች የባለ-አደራ ቦርድ አባላት በጠቅላላው የአባልት ስብሰባ ይመረጣሉ። በአባል ከሥራ ስንብት ምክንያት ክፍት ቦታ ቢኖር፣የ (ኢሲኤኤስ ዳይሬክተሮች ቦርድ እስከቀጣዩ ጠቀላላ ስብሰባ ድረስ ተተኪ ባለአደራ አባላትን መሙላት ይቻለዋል።

ለ) ከአባላት መሃከል ለባለ-አደራ ቦርድ አባልነት የሚመረጡ ት አምስቱ (5) እጩዎች ለ ሰባት (7) ዓመታት ያገለግላሉ።

ሐ) የባለአደራ ቦርድ አባላት፣ የሥራ ዘመናቸው ሲያበቃ፣ በድጋሚ ተመርጠው ለማገልገል የሚያግዳቸው አይኖርም።

መ) የኢሲኤኤስ ዲሬክተሮች ቦርድ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሁለት (2) የባለ-አደራ ቦርድ እጩዎች ስም ጠቁሞ መምረጥ ይችላል። እነህም ሁለት ተመራጮች ለአምስት (5) ዓመታት የሥራ ዘመን ያገለግላሉ። አግልግሎታቸውም ለ(ኢሲኤኤስ) የሚበጅ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ፤ የዲሬክተሮች ቦርድ የእኝሁኑ ባለአደራ-ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን በተጨማሪ አምሥት (5) ዓመታት ማራዘም ይችላል።

ECS Bylaw First Draft

**5.3** የባለ-አደራ ቦርድ ሃላፊነትና ዋና ተግባራት

ባለ-አደራ ቦርድ ዋነኛ ሃላፊነታቸው በ(ኢሲኤስ) መተዳደሪያ ደንብ በተጠቀሰው መሠረት የማሕበሩን ንብረትና ሃብት ማስጠበቅና ማስከበር ይሆናል። ይህም ሃላፊነት፤

ሀ) የ(ኢሲኤስ) ንብረትን በሙሉ በያለበት መንከባከብና በወግ ማስጠበቅ፤

ለ) ንብረቶች ሁሉ ለአደጋ አለመጋለጣቸውን እያስተዋሉ ማረጋገጥ፤

ሐ) ንብረቶቹ ሁሉ ከከስ፣ ከተፈጥሮ አደጋ፣ ከሌላም በኩል ለሚሰነዘረው፣ ወይም ሊደርስ ከሚችለው ጉዳት በሙሉ ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ፤

መ) ንብረቱ አገልግሎት ላይ በሚውልበት ጊዜ፣ አስፈላጊው ሕጋዊ ጥንቃቄ ሁሉ መደረጉንና መሟላቱን ማረጋገጥና ማስከበር የመሳሰሉትን ሁሉ ያካትታል።

## አንቀጽ 6

### የማሕበሩ አማካሪ ሸንጎ

6.1 አመሠራረት

የኢሲኤስ ዳይሬክተሮች ቦርዱ ለአማካሪ ሸንጎ አባልነት እንዲመረጡ የሰባት (7) እጩዎችን ስም ለጠቅላላ ስብሰባ ይጠቁማል :: ከሰባቱ መሃል አምስቱ (5) በጠላላ ጉባኤ ተመርጠዉ ለሶስት (3) ዓመታት እንዲያገለግሉ ይሾማሉ።

6.2 የማሕበሩን እድገትና መዳበር አስመልክቶ የኢሲኤስ ዳይሬክተሮች ቦርድ በሚጠይቀው መሠረት፤ የአማካሪው ሸንጎ ለማህበሩ እድገት የሚበጁ ማሻሻያ ሃሳቦች ማቅረብ ይችላል።

6.3 አማካሪው ሸንጎ፤ስለማሕበራዊ ኑሮ፣ ስለባሕል፣ ትምሕርትና፣ ሕግ-ነክ ጉዳዮች ሁሉ፣ የኢሲኤስ ዳይሬክተሮች ቦርድን ያማክራል።

6.4 በኢሲኤስ ቦርድ አባላትና፣ ወይም በቋሚ ኮሚቴ አባላት መሃከል፣ አለያም በጠቅላላው ጉባዔ መሃከል አለመግባባት ቢፈጠርና ሁከት ቢነሳ፣ የማሕበሩ አሠራር ቢተጓጎል፤ አማካሪው ሸንጎ በአስታራቂነት ሃላፊነቱን ወስዶ፤ አወዛጋቢ ችግሮችን በማስወገድ አባላቱን ያስማማል።

## አንቀጽ 7

### ቋሚ -ኮሚቴ

7.1 ሥራ አስፈፃሚ (ኤክዜኪውቲቭ) ኮሚቴ

ECS Bylaw First Draft

ፕሬዚዳንቱ/ትዋ፣ ም/ፕሬዚዳንቱ/ትዋ፣ ዋና ፀሓፊው፣ ገንዘብ-ያዥና የሕዝብ-ግንኙነት ሹሙ ያሉበት ኮሚቴ ሥራ-አስፈፃሚ (ኤክዜኪውቲቭ) ኮሚቴ ይሆናል።ሥራ እስፈፃሚው ኮሚቴ በመተዳደሪያው ደንብ መሠረት፣ለዲሬክተሮች ቦርዱ ካልተከለለው በስተቀር፤ የማሕበሩን ቀን-ተቀን ጉዳይ ሁሉ የማስፈፀም ሓላፊነት አለበት። የማሕበሩ ፕሬዚዳንት፣ ሥራ-አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባ ለመጥራትና መምራት ይችላል። የሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴው ስብሰባ፣ ከአምስቱ ተሳታፊዎች መሃል ሦስቱ ብቻ ከተገኙ፣ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።

**7.2** የዳይሬክተሮች ቦርድ ለሥራ አፈፃጸም የሚያመች ሆኖ ካገኘው የሚመሠረተውን ኮሚቴ ተግባራትና ሃላፊነት ሊለውጥና ሊያሻሽል ይችላል። እንደሁኔታው አስፈላጊነት ቦርዱ አዲስ ኮሚቴ መመሥረትና ያሉትንም አቀናጅቶ ማዋሐድም፣ሆነ ማጠቃለል ይችላል።

**7.3** በቦርዱ ካልቀረበ በስተቀር፣ የማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ሥራ እስፈፃሚ (ኤክዜኪውቲቭ) ኮሚቴ ስብሰባ በፕሬዚዳንት ጠያቂነት፣ ለአባላት በፅሁፍ ወይም በቃል፣ በሃያ አራት (24) ሰዓት ማስታወቂያ፣ሊጠራ ይችላል።በማንኛውም ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ይበልጡ ከተገኙ፣ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።

## አንቀጽ 8

### ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ (ጉባዔ)

**8.1** የማሕበሩ ቦርድ በዓመት ቢያንስ አንድ (1) ጊዜ ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ይጠራል። በጠቅላላው ሰብሰባ ለመሳተፍ የሚችሉት፣ ከዚሁ ስብሰባ (24) ሰዓት አስቀድመው፣ በቋሚ አባልነት ተመዝግበው ጸንተው የቆዩ አባላት መሆን ይኖረባቸዋል።

**8.2** ዓመታዊ ጠቅላላ ስበሰባ፣ ሂሳብ ማጠቃለያ (መዝጊያ) ወር ካለፈ በቀጣዩ ስድሳ (60) ቀናት ውስጥ እንዲደረግ አስፈላጊ ይሆናል።

**8.3** የማሕበሩ ጠቅላላ ስብሰባ፤ የዳይሬክተሮችን ቦርድ ወይም የባለአደራ-ቦርድን አምስት፤እና የሂሳብ መርማሪ ኮሚቴ አባላትን ጭምር፤ ለመምረጥም ሆነ ተገቢ ሆኖ ካገኘው፣ በበቂ ምክንያት፣ በአግባቡ ሽሮ ማሰናበት ይችላል። ሆኖም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ፣የማሕበሩ አባላት በማሕበሩ ስም ቦርድ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውጪ፣ማሕበሩን የሚወክሉበት ምንም ሌላ ሥልጣን አይኖራቸውም።

**8.4** ይህን የማሕበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለመሻርም ሆነ ለማሻሻል የብዙሃኑ

ሀ) የ(ኢሲኤስ) የማሕበሩ አባላት ፈቃድ ያሰፈልጋል።

ለ) ማሕበሩን ከሌላ ማሕበር፣ ወይም ድርጅት ጋር ለማዋሃድም (ለማደባለቅም) ሆነ ለማቀናጀት፤

ECS Bylaw First Draft

ሐ) ማሕበሩን በውዴታ (በፍቃድ) ለማፍረስም፤

መ) የማሕበሩን ንብረትና ንዋይ፣ ለመሸጥ፣ ለረጂም ጊዜ ለማከራየትም ሆነ በሌላ ንብረት ለመለወጥ፤የጠቅላላው አባላት ፈቃድና መስማማት አስፈላጊ ነው።

**8**.5 የጠቅላላው ዓባላት ስብሰባ ምልአተ-ጉባኤ የሚሟላው ከቋሚ አባላቱ ከመቶው 51% (51 ከመቶው) ወይም ከዚያ በላይ ሲገኙ ነው።

## አንቀጽ 9

## ለምርጫ አስፈላጊዎቹና የአፈፃጸምና ሥርዓት

9.1 ቦርዱ ከምርጫው ዕለት ኣራት (4) ሣምንታት አስቀድሞ፣ ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ይጠራል።

9.2 ቦርዱ ሦስት አባላት ለአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት የሚጠቆሙ ስም እንዲያዙና፣ ምርጫ እንዲያስፈጽሙ በድምሩ ሰባት (7) አባላትን መርጦ፣ አስመራጭ ኮሚቴ ይመሠርታል።ቦርዱም አስመራጭ ኮሚቴ መመሪያ ይሰጣል።

9.3 ቦርዱ ለተመራጭነት እጩነት ስም መጠቆሙን አስመልክቶ፣ቀኑን፣ ሥፍራውን፣ ለአባላት ሁሉ በሚገባው መሠረት በይፋ እንዲታወቅ፤ ቢያንስ ኣሥራአራት (30) ቀን አስቀድሞ የምርጫውን ቀን ያስታውቃል። (በተጨማሪም ሰለዚሁ የሚወጣውን፣ አባላት ሁሉ እንዲያዩት በማሕበሩ አዳራሽ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል)።

9.4 ቦርዱ ምርጫው ያለምንም ችግር በትክክል እንዲካሄድ፣ በሚያስፈልገው ረገድ፣ ሁሉ ከአስመራጭ ኮሚቴ ጋር ይተባበራል።

9.5 ማንኛቸውም ሁለት ድምጽ ለመስጠት ብቁ የሆኑ የማሕበሩ አባላት፣ ከምርጫው ሁለት ሳምንት አስቀድመው ለአስመራጭ ኮሚቴ በእጩነት የአባል ስም ሊጠቆሙ ይችላሉ።

9.6 የምርጫ ድምጽ የሚሰጠው በምስጢር ይሆናል። ድምጽ ለመስጠት፡ አባል በአካል መገኘት አለባቸው። በምርጫው ላይ ሳይገኙ፣ በመልክት ወይም በሌላ ዘዴ መምረጥ አይቻልም።

9.7 ከማንኛውም ምርጫ በፊት፤ቢያንስ ለ ስድስት ወራት (6 ወር) ተገቢውን የአባልነት ክፍያ አሟልተው በማሕበሩ እንቅስቃሴ በወግ የሚሳተፉ ቋሚ አባላት ብቻ ድምጽ መስጠት ብቃት ይኖራቸዋል።

ECS Bylaw First Draft

## አንቀጽ 10

### መርማሪ (አጣሪ) ኮሚቴ

በማህበሩ ጠቅላላ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ፤ ሦስት (3) አባላት የሚኖሩት መርማሪ (አጣሪ) ኮሚቴ ይመረጣል። ይህም መረማሪ (አጣሪ) ኮሚቴ፣ የማሕበሩን ንብረትና ሂሳብ መዛግብት ሁሉ መርምሮ አያጣራ፤ የምርመራውን ውጤት፣ በየዓመቱ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ለአባላት ማቅረብ ይኖርበታል።የማሕበሩ (የኢሲኤስ) ሥራ ክንውን እያደገ ሲሄድ፣ በማሕበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ወቅት፣ ከማሕበሩ አባላት ውጪ፣ ባለሙያ ሂሳብ መርማሪ የመቅጠር ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል።

የማሕበሩ(የኢሲኤስ) መረማሪ ኮሚቴ፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ በኢመማ (ማሕበሩ) መተዳደሪያ ደንብና በተገቢው ሂሳብ አሠራር መሠረት፣ የማሕበሩን ሂሳብ መዛግብትና ደረሰኞች፣ ተከፋይ (ወጪ) ቼኮች ሁሉ በተክክል መሠራታቸውን መመርመር አለበት።

## አንቀጽ 11

### የማሕበሩን ደንብ ማሻሻል

11.1 ከዚህ ቀድሞ ማሕበሩ ይሠራበት የነበረው (እንደአውሮፓ አቆጣጠር 2001 ዓም) ሥራ ላይ የዋለው የማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ እነሆ በዚህ በያዝነው መጋቢት ወር 2004 ዓም (በአውሮፓ አቆጣጠር ማርች 2012) ተሻሽሎ ተተክቷል። ሰለሆነም፣ በዚህ መተዳደርያ ደንብ የተካተቱት ስምምነቶች፣ ውለታዎችና ግዴታዎች፣ መብቶች ከላይ እንደተጠቀሰው የማሕበሩ (የኢሲአኤስ) ጉዳዮች ናቸው።

11.2 ለወደፊቱ፣ ሰላሳ (30) ወይም ከዚያም በላይ በሆኑ አባላት የደንብ ማሻሻያ ጥያቄዎች ሁሉ በጽሑፍ ለዋናው ጸሓፊ፣ ከቀጣዩ ጠቅላላ ሰብሰባ ቢያንስ ሰላሳ (30) ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ለአባላት ሁሉ ተበትኖ መዳረስና መቅረብ ይኖርበታል።

11.3 የማሕበሩን ደንብ ማሻሻል ሃሳብ፣ በስብሰባው መድረክ ላይ ከአባላት ሊቀርብ ይችላል።

11.4 በድፍኑ የማሕበሩን መተዳደሪያ ደንብ የመሻር፣ የማውደቅ ጥያቄም ሆነ፣ ወይም በሙሉ አለያም በከፊል እንዳለ ሙሉ አንቀጽ ገንጥሎ የማወጣት ሃሳብ፣ ከአባላቱ በ (2/3) በሁለት-ሦስተኛው ድምጽ ካለተደገፈ በስተቀር፤ ተቀባይነት አይኖረውም።

## አንቀጽ 12

### የሂሳብ ዓመት (ዘመን)

ECS Bylaw First Draft

12.1 የማሕበሩ የ(ኢሲኤስ) የሂሳብና የሥራ ዓመት እንደሃገሩ አሠራር ሁሉ፣ ከጃንዋሪ 1 (አንድ) ቀን ጀምሮ እስከዲሴምበር (31) ቀን ድረስ ይሆናል።

12.2 የማሕበሩ የ(ኢሲኤስ) ሂሳብ መዛግብትና ደርሰኝ፣ የወጪ ሰነዶች ሁሉ፣በአንቀጽ 11 በተቀሰው መሠረት፣ ብቁ በሆነ የሂሳብ ምርመራ ባለሙያ መጣራት አለባቸው። በሂሳብ መርማሪው የተጣራው ሰሌት፣ በዳይሬክተሮች ቦርዱ በዓመታዊ ጠቀላላ ስብሰባ ላይ ለአባላት በይፋ መታወቅ አለበት።

## አንቀጽ 13

### ከሃላፊነት መከለልና (ከከስ -ነጻ የመሆን ብቃት)

13.1 የማሕበሩ የ(ኢሲኤስ) ዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ባለአደራ-ቦርድ፣ የሥራ ሹሞችም ሆኑ፣ ሌሎች የማሕበሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ሁሉ የማሕበሩን ጉዳይ በሚያስፈጽሙበት ሥራ በሚያከናውኑበት ጊዜ ስለሚደርስ አንድ አንድ ሰበብ፤ በግል ተጠያቂ ሆነው ሊያስከስሳቸው አይችልም።ይሁን እንጅ፣ በቸልተኝነትም ሆነ በተንኮል፣ ኣለያም ሃላፊነትን ባለማክበር፣በማሕበሩ ደንብ መሠረት በተሰጠው/ጣት ሥልጣን በመባለግ ሥራውን በደለ/ለች ተብሎ የተበየነበት/ባት ግን በፈጸመው/መችው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል/ትሆናለች።

13.2 ማሕበሩ አግልግሎቱን የሚሰጠው (የሚያቀርበው) ለትርፍ ወይም ገንዘብ ለማፍራት እይሆንም። ማሕበሩ የሚያገኛቸው ማናቸውም ገቢዎች ሁሉ፣ የቆመበትን ዋና ዓላማውን ለማራመድ ብቻ በሥራ ላይ ይውላሉ።

13.3 የቦርድ ዳይሬክተሮችና ሌሎችም የሥራ አመራር እባላት ሁሉ፣ ማሕበሩን የሚያገለግሉት፣ በበጎ ፍቃድ ያለደመወዝ በነፃ መሆን አለበት። ቦርድ-አባላትም፣በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልክ በቦርድ አባልነታቸው ተጠቃሚ መሆን አይቻላቸውም። ሆኖም ሥራቸውን ለመፈጸም የሚያወጡትን ተገቢ ወጪ፣ የማሕበሩ የገንዘብ አቅም ከፈቀደ፣እንደሥራ ማሰኬጃ ሊከፈሉት ይቻል ይሆናል።

## አንቀጽ 14

### የማሕበሩ አባልነት

14.1 ማንኛውም ሰው በማሕበሩ በ (ኢሲኤስ) መሠረታዊ ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ የተጠቀሱትን ደንብና ሥርዓቶች ሁሉ ተስማምቶ ተገቢውን የአባልነት ከፍያ የሚከፍል፣ ዓላማዎችን የሚደግፍ ከሆነ፣የማሕበሩ የ(ኢሲኤስ) ኣባል መሆን ይችላል።

ECS Bylaw First Draft

14.2 <u>ቋሚ አባል</u፤ የሚባል አባል፣ የማሕበሩን ቋሚ የአባልነት መዋጮ በወቅቱ የከፈለና በማሕበሩ እንቅስቃሴዎች አዘውትሮ የሚሳተፍ ግለ-ሰብ ወይም ቤተ-ሰብ ነው።ቤተ-ሰብም የሚባለው አባሉና ባለቤቱ/ትዋ ሲሆኑ ህጻናት ልጆችም ካሉዋቸው አብረው አባል ይሆናሉ።

14.3 <u>ደጋፊ አባል</u>፤ የማሕበሩን (የኢሲኤስን) ዓላማ በመደገፍ፡ ማሕበሩ የሚያከናወናቸውን እንቅስቃሴዎች ለመርዳት፣ የገንዘብም ሆነሌላ ቁሳቁስ እርዳታ የሚለግሱ፣ የማሕበሩ ደጋፊ አባላት ናቸው። ደጋፊ አባላት፣ ድምጽ የመስጠትም ሆነ ለምርጫ እጩ   ሆነው መቅረብ  አይችሉም።ይሁን እንጂ፣ በጠቅላላ ስብሰባ ላይ ለመገኘትም ሆነ በግል በእንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላሉ።የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የደጋፊ አባላትን ማመልከቻዎች አስተውሎ፤ ሃላፊነትና ተግባር መለወጥ፣ ማሻሻል ማጽደቅ ይችላል።

14.4 <u>የክብር አባላት</u>፤ የማሕበሩ የክብር አባል የሚባለው፣ ለማሕበሩ ከፍተኛ የሆነ የድጋፍ አስተዋጽዖ ያደረገ ግለ-ሰብ ወይም ቤተ-ሰብ፣ ወይም የራሱ አባላት ያሉት ድርጅት ነው። ቦርዱ ለክብር አባልነት ብቃት አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን አባላት ለይቶ በማውጣት ስማቸውን ለጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባው እንዲያጸድቅለት ያቀርባል። የክብር አባላት የሆኑ ሁሉ፣ ለማሕበሩ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ ከፍተኛ ሰለሆነ፣ የማሕበሩን የዓመት ክፍያ ወይም የወር መዋጮ የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም። እንደ ደጋፊ አባላት ሁሉ፣ የክብር ደጋፊዎች፣ የመምረጥ ድምጽም ሆነ፣ለተመራጭነት እጩ ሆነው መቅረብ አይችሉም። ይሁንእንጂ፣ በስብሰባ ላይ መገኘትም ሆነ በየእንቅስቃሴዎች ከመሳተፍ አይታገዱም።

14.5 ከአባልነት መሰናበት ማንኛውም አባል ከማሕበሩ አባልነት ያለምክንያት በፈቃዱ መሰናበት ይችላል።

14.6 የአባልነት ክፍያ መተጓጎል፤ አንድ አባል (90) ከዘጠና ቀናት በላይ የአባልነት ክፍያ አለመክፈል፣ አንድን አባል ከማሕበሩ (ኢሲኤስ) አባልነት ደረጃው ሊያወርደው ወይም አባልነቱን ጭራሹን ሊያሳጣው ይችላል።

14.7 የማሕበሩ አባልነት ክፍያ መጠን አንደሁኔታው እየታየ በቦርዱ ይወሰናል።የቦርዱም ውሳኔ አባላቱ እንዲያስተውሉት፣በጠቅላላው ስብሰባ ጊዜ ይቀርባል። ማንኛውም ለማሕበሩ የተከፈለ መዋጮም ሆነ የገንዘብ ሥጦታ፣ እንዴ ለማሕበሩ ከገባ በኃላ፣ ተመላሽ አይሆንም።

14.8 ቦርዱ በቂ ምክንያት ካገኘና፣በአድራጎቱ ማሕበሩን (ኢሲኤስ)ን  የሚጎዳ ከመሰለው፤ ማንኛውንም ሰው ከአባልነት ማስወገድ (ማግለል) ይችላል፡ በዚህ መሰል ሁኔታ ከአባልነት ይሚወገደው ሰው፤ ሰለራሱ/ራስዋ መወገድ በሚካሄደው ጠቅላላ ስብሰባ (ውይይት) ላይ የመገኘት መብት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 15

የጥቅም ግጭት (መፃረር)

ECS Bylaw First Draft

15.1 ማንኛውም የቦርዱ አባል፣ የባለአደራም ሆነ የሌላው የማሕበሩ-ቦርድ አባል፣ ወይም የማሕበሩ ሠራተኛ፣ ከማሕበሩ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ወይም የሚፃረር፣መስሎ ከሚታይ ሥራቸውን ከአድሎ ነጻ በሆነ መልክ ለመፈጸም በማይችሉበት ተግባር ውስጥ ከመሳተፍ የታገዱ ይሆናሉ። ይህንኑም ለቦርዱ እሳውቀው፣ ውይይት ከመካሄዱ፣ ወይም ድምጽ ከመስጠቱ በፊት በፈቃዳቸው ተግልለው፣ እራሳቸውን በይቅርታ ያወጣሉ።

የሚከተሉት ሁኔታዎች የጥቅም መጻረር የሚኖርባቸው ይሆናሉ፤

ሀ) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ተቀጣሪ የማሕበሩ ሠራተኞችም ሆኑ፤ የበጎ ፍቃድ አገልጋዮችም ጭምር ሆኑ ዘመዶቻቸው፤ ከኢሲኤስ ጋር ሥራ የተቋረጠ፤ አገልግሎት ሊሰጥ የተስማማ፤ ውል የተዋዋለ፤ ድርጅትም ሆነ ሌላ አካል ከሆኑ፤

ለ) የማሕበሩ ዳይሬክተርም ሆነ፤ ሹም፤የበጎ ፍቃድ አገልጋይም ጭምር፤ ወይም፤ ዘመድ ሁሉ፤ ከኢሲኤስ ጋር የስራም ሆነ ሌላ ውል ካለው አካል ጋር የገንዘብም ሆነ ሌላ ጥቅም ተጋሪ አካል ሽርካ ወኪል፤ ወይም ጥቅም አስከባሪ ከሆነ፤

ሐ) የማሕበሩ ዳይሬክተርም ሆነ፤ ሹም፤የበጎ ፍቃድ አገልጋይም ጭምር፤ ወይም፤ ዘመድ ሁሉ፤ ከኢሲኤስ ጋር ከሚወዳደር ደረጅት ጋር ግንኙነት ገንዘብ-ነክ አለያም ሌላ የጥቅም ትስስር ካላቸው፤

መ) በስጦታም መልክ ሆነ በሌላ ዓይነት የሚቀርብ መታያ መሰል የመዝናኛም ግብዣ ሁሉ የአንድን ቦርድ አባል፤ ሹም፤ ሰራተኛ፤ ወይም የበጎ-ፍቃደኛ አገልጋይ፤ ሃሳብ ለማስለወጥ፡ የሥራ አመላካከት ለማስቀየር የሚሰነዘር ቸሮታና ምንም አንሶም የሚታይ ስጦታም ቢሆን፤ ከኢሲኤስ ተግባራት ጋር የተያያዘ ባይመስልም አንኳን ስጦታና እጅ-መንሻ መቀበል፤

ሠ) በማሕበሩ (በኢሲኤስ) የገንዘብ አወጣጥ ላይ የመወስን ሥልጣን ባለው ሹምም ሆነ በሌላም ይህንኑ መስለው ሊታዩ የሚችሉ ሁኔታዎች ከተከሰቱ፤

15.2 ማንኛቸውም የጥቅም መጻረር ሁኔታዎች ሁሉ ለማሕበሩ ቦርድ አባላትና ሠራተኞች ሁሉ በሚገባው መልክ በይፋ ተገልጸው፤ የማሕበሩን ሕልውና ለማስጠበቅ ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ውሳኔ ማለፍና መጽደቅ ይኖርበታል።

15.3 ምስጢር አጠባበቅ፤ እያንዳንዱ ሹም፤ የቦርድ ዳይሬክተር፤ ተቀጣሪ ሠራተኛም ሆነ የበጎ ፍቃድ አገልጋይ ሁሉ፤ ሰለጥቅም መጻረር ሆነ ስለሌም የማሕበሩ ምስጢሮች አጠባበቅ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተለይም ማሕበሩ ላይ ጉዳት እንዳይደርስም የማሕበሩ ዓላማ እንዳይሰናከል መጠንቀቅ

ECS Bylaw First Draft

ያሻዋል።

15.4 የማሕበሩ ቦርድ ከላይ የተጠቀሰውን የጥቅም መጻረር አስመልክቶ፡ በሚገባ መልኩ እንደሚያስፈልገው የውስጥ አስተዳደር መመሪያ ማወጣት ይኖርበታል።

## አንቀጽ 16

### የማሕበሩ መፍረስ (መዘጋት)

16.1 ማሕበሩ (ኢሲኤስ) ሊፈርስ የሚችልበት ሁናቴ እንደሚከተለው ከሆነ ብቻ ይሆናል።

16.2 የማሕበሩ ጠቅላላ አባላት በማያወላውል ድምጽ እንዲፈርስ ተስማምተው ሲወስኑ፣እና

ሀ) የባለአደራ ቦርድ

ለ) የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሐ) ከአባላቱ ሦስት-አራተኛው (3/4) ተስማምተው በአንድነት መፍረሱን ሲያጸድቁት

16.3 ይህ ከሆነና ማሕበሩ በእርግጥ ከተዘጋ፣ ማሕበሩ (ኢሲኤስ) ያለበት እዳዎችና ግዴታዎች ተከፍለው፣ ተራፊ የሚቀረው ገንዘብና ንብረቶች በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ላሉ የዚሁ ማሕበር ዓይነት ዓላማ ለሚያካሂዱ በጎ አድራጊ ድረጅቶች ይከፋፈላል።

ECS Bylaw First Draft